ማጂክ ካርፔት ት/ቤት አማርኛ ሞዴል ፈተና ለ8ኛ ክፍል

ምንባብ

የሰው ልጅ ምግብ አብስሎ ለመብላት እና ራሱን ከአደጋ ለመከላከል እሳት ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ የስራ ፈጠራ ባለቤት ነበር ብሎ መናገር ይቻላል።በጥንታዊው የሰው ልጅ የአኗኗር ስርዐት ውስጥም ከተፈጥሮ ጋር በነበረው ግኑኝነት ራሱን ለማኖር ደመነፍሳዊ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ወጥቶ የድንጋይና የእንጨት መሣሪያዎችን መጠቀም በጀመረበት ጊዜ የስራ ፈጠራ ነበር። በጊዜ ሂደትም ትናንሽ ከምንላቸው የፈጠራ ስራዎች ጀምሮ ታላላቅ እና እጅግ አስደናቂ የሚባሉ በርካታ ፈጠራዎችን አከናውኗል።

የስራ ፈጠራ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የማፍለቅ ወይም የመፍጠር ጥበብ ነው።በአገራችን የአክሱም ሀውልት፣የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን፣የሀረር በርና ሌሎችን ማየት ለፈጠራ በቂ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል።ይህም ኑሮን በተሻለ ለመኖርና ጣፋጭ ለማድረግ ካለን የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ከሆነ ባህሪ የሚመነጭ ነው። በሌላ በኩል አዲስ ነገርን መፍጠር አሁን አገለግሎት የሚሰጠንን የፈጠራ ስራ በተሻለ መንገድ አገልግሎት ሊሰጠን በሚችል ሁኔታ እንደገና አሻሽሎ መስራትም ነው።በሌላ አገላለጽ በኑሮ ሂደት የሚያጋጥሙ ውጣውረዶችንና ችግሮችን በማቃለል ኑሮን ቀላል ማድረግ ነው።ቀደም ሲል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ በእግር በኋላም በፈረስና በበቅሎ የመጓዝ ሁኔታ ነበር።በዚህ ዘመን ደግሞ እጅግ ፈጣንና ምቹ የሆኑ የምድር፣የባህርና፣በአየር የሚንቀሳቀሱ በርካታ የትራንስፖርት መገልገያ መሣርያዎች ተፈጥረዋል። ይህም ቀደም ሲል እናጠፋው የነበረውን ጊዜ ገንዘብና ጉልበት በመቀነስ በፈለግነው ጊዜ የፈለገው ቦታ ያለምንም ድካም በመድረስ የምንፈልገውን ተግባር እንድናከናውን አስችሎናል።

በአንድ ሀገር የስራ ፈጠራ መስፋፋት ወሳኝ ነገር ነው። የስራ ፈጠራ እንዲስፋፋ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች መኖር አለባቸው። እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ውስጣዊም ውጪያዊም ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህ ምቹ ሁኔታዎች መካከል የዜጎች የስራ ፍቅርና ተነሳሽነት እንዲሁም ለዘርፉ መስፋፋትና አለመስፋፋት ላይ የተመሠረተ ነው። ለእድገት ዋና መሠረት የስራ ፈጠራ መሆኑን በአግባቡ የተረዱ ለስራ ፈጠራ ትልቅ ግምትና ትኩረት ይሰጣሉ። የስራ ፈጠራ እንዲያድግና እንዲስፋፋ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ።

በተለይ አሁን ባለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን የገበያ ፍላጎት ተለዋዋጭና እጅግ ፈጣን እንቅስቃሴ በሚታይበት ኢኮኖሚ ውስጥ ያለስራ ፈጠራ በገበያ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ መሆን አይቻልም። የደንበኞች ፍላጎት የቴክኖሎጂውን ምጥቀት እየቀደመ ቴክኖሎጂው የደንበኞችን ፍላጎት አስቀድሞ በመተንበይ አዳዲስ የስራ ፈጠራዎችን ወደ ገበያ እያቀረበ በገሰገሰ ቁጥር የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብን መላበስ የበለጠ ጠቀሜታ አለው።

ምንጭ፣ ተፈራ ሙሉነህ ።ሺ፪ሺ።የሥራ ፈጠራና የብልጽግና ጥበብ ።አዲስ አበባ ፣ሜጋ አሳታሚ የግል ማህበርከገጽ ፪-፮

በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ።

መመሪያ ፩፦ ከጥያቄ ቁጥር ፩ -፲ ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

_____ ፩.በምንባቡ የመጀመሪያ አንቀፅ ውስጥ በዕውቀትና በጥበብ አለመመራትን የሚመለከተው ቃል የትኛወው ነው?

ሀ. ጥንታዊ ሐ. ተፈጥሯዊ

ለ.ደመነፍሳዊ መ.ሥርዓታዊ

_____ ፪.የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ትኩረት የሚያደርገው ስለምንድን ነው?

ሀ. ስለ ሰው ልጅ ታሪክ ሐ.ስለ ሥራ ፈጠራ

ለ.ስለ አደጋ መከላከል መ.ስለ ጥንታዊ ሰው

_____ ፫.በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የሰው ልጅ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስን ቀለል ለማድረግ የተጓዘበትን መንገድ የሚያሳየው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ.አንድ እግር፣ሁለት እግር፣ አራት እግር፣በአየር መጓዝ

ለ.በታክሲ፣ በአውቶቢስ ፣በባቡር፣ በአየር፣በአየር መንገዝ

ሐ.በብስክሌት፣በእግር፣በመኪና፣በመርከብ፣በአየርመንገዝ

መ.በእግር፣በበቅሎ፣በመኪና፣በመርከብ፣ በአየር መንገዝ

_____ ፱.አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ሥራ ላይ የማዋል ጥበብ እንደሆነ ተደርጎ የተገለጸው ምንድን ነው?

ሀ.የሥራ ሂደት ሐ.የፈጠራ ስራ

ለ.የትራንስፖርት መገልገያ መ.የአክሱም ሀውልት

_____ ፲.ለሥራ ፈጠራ መስፋፋት እንደምቹ ሁኔታዎች የተጠቀሱት ምንድን ናቸው?

ሀ.የዜጎች የሥራ ፍቅርና የመንግስት ፖሊስ

ለ.የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን መሟላት

ሐ.የቴክኖሎጂና የደንበኞች ፍላጎት

መ.የዜጎች ተነሳሽነትና የገበያ ፍላጎት

_____ ፲፩.በሀገራችን መካከል ለሚታይ የዕድገት ልዩነት እንደምክንያት ተደርጎ የተወሰደው ምንድን ነው?

ሀ.የቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ውስጥ መግባትና አለመግባት

ለ.የትምህርት ስራ እንቅስቃሴ መዳበርና አለመዳበር

ሐ. የስራ ፈጠራ መስፋፋትና አለመስፋፋት

መ.የስራ ፍጥነትና ዝግመት

_____ ፲፪.የቴክኖሎጂ እድገት የደንበኞችን ፍላጎትአርክቶ መገኘት እንዳለበት የሚገልጸው አንቀጽ የትኛው ነው?

ሀ.አንደኛው ለ.ሀለተኛው ሐ.ሦስተኛው መ.አራተኛው

_____ ፲፫.ለቀረበው ምንባብ ርዕስ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው? ሀ.የቴክኖሎጂ መስፋፋት ሐ. የገበያ ፍላጎ

ለ. የስራ ፈጠራ መ.የዕድገት ጎዳና

_____ ፲፬.በምንባቡ መሠረት የስራ ፈጠራ ለዕድገት መሠረት መሆኑን የተረዱ ሀገሮች ምን ያደርጋሉ?

ሀ.ለስራ ፈጠራ ትኩረት ይሰጣሉ፤ድጋፍም ያደርጋሉ።

ለ.ፋብሪካ ይገነባሉ፣ ምርት ይሰበስባሉ።

ሐ.ገበያ ያስፋፋሉ ድህነትን ይጠየፋሉ።

መ.የስራ ተነሳሽነት ያሳያሉ።

_____ ፲.በሀገራችን ለፈጠራ ስራ በምሳሌነት ስለተጠቀሱት ነገሮች የሚናገረው ስንተኛ አንቀጽ ነው?

ሀ.አንደኛው ለ.ሁለተኛው ሐ.ሦስተኛው መ. አራተኛው

መመሪያ፤= ከተራ ቁጥር ፲፭-፳ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ ምረጡ።

_____፲፭ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ቁጥርን አመልካች ነው።

ሀ.ፊሪዎች ለ.ጻድቃን ሐ.ካህናት መ.ሁሉም መልስ ይሆናል።

_____፲፮. እግረኛ በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው ቅጥያ ዋና ቃሉ ምንን እንዲገልጽ አድርጎታል?

ሀ. በእግር ተጓዥ መሆንን ሐ. ሯጭ መሆንን

ለ. ሠልፈኛ መሆንን መ. የእግር ኳስ ጠባቂ መሆን

_____፲፫. አቶ ዮሐንስ ሽምግልና አለባቸው። የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ትርጉም _____ነው።

ሀ.እርጅና ለ.ድክመት ሐ.ዳኝነት መ.እርቅ

_____፲፬. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ድርጊታዊ ተቃርኖን (አለመመሳሰልን) አይገልጽም።

ሀ.ተኛ- ተነሳ ሐ. በላ-ተመገበ

ለ. ወደደ-ጠላ መ.ዋጠ-ተፋ

_____፲፭. ከሚከተሉት አያያዥ ቃላት መካከል አፍራሽ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.ስለዚህ ለ.ግን ሐ.ከዚያ በኋላ መ. በመሆኑም

_____፲፮. ሆደሰፊ ለሚለው ፈሊጥ ትርጓሜው፦ _____ነው።

ሀ.ሆድ ትልቅ የሆነ ሐ. ወፍራም

ለ. ታጋሽ መ.ቶሎ የሚቀየም

_____፲፯ ልብ ገዛ ለሚለው ፈሊጥ ትርጓሜው _____ነው።

ሀ.ልብ ተበረከተለት ሐ. ማስተዋል ጀመረ

ለ. ልብ አገኘ መ.ማስተዋል ከበደው

_____፲፰. አላልኩህም! ሰውዬው መጥቷል ። ይህ ዐ.ነገር የቀረበበት ስልት _____ነው።

ሀ.በአሉታዊ ሐ. በጥያቄያዊ

ለ. በትዕዛዛዊ መ.በአጋኖአዊ

_____፲፱. እረኛ መንጋውን ይጠብቃል።የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የስም ዓይነት ይመደባል?

ሀ.ከወል ለ. ከረቀቂ ሐ. ከተጸውኦ መ.ከጥቅል

_____፳. የምትወዱትን ምግብ በላችሁ።በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ባለቤት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ.እኛ ለ. እሳቸው ሐ. እናንተ መ.እነሱ

መመሪያ፫፦ከጥያቄ ቁጥር ፳፩-፳፭ ድረስ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ናቸው ተብለው ከተሰጡት አማራጮች መሀከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

_____፳፩.ዋልጌ

ሀ.ነውረኛ ለ.ባለጌ ሐ.የማይጠቅም መ.ጨዋ

_____፳፪.እምብርት

ሀ. ዙርያ ለ.ዳር ሐ.መሀል መ.ገደል

_____፳፫.የበኩር

ሀ.የመሀል ለ.የመጀመሪያ ሐ.የመጨረሻ መ.አዋቂ

_____፳፬.ቁጥብ

ሀ.ልቅ ለ.ድብቅ ሐ .ምስጢረኛ መ.ስውር

_____፳፭.ሰርክ

ሀ.ዘወትር ለ.ሁልጊዜ ሐ.በዓል መ.የተለመደ

መመሪያ፬፦ ከተራ ቁጥር ፳፮-፴፭ ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ ምረጡ።

_____፳፮.ክፉ ነገር አትናገረኝ አይገቡ ገብቼ እከፍላለሁ። ለተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር የማይስማማው ፍቺ የትኛው ነው?

ሀ.ወጥቼ ወርጄ ሐ.ገብቼ ወጥቼ

ለ.አይሆኑ ሆኜ መ.የትም የትም ብዬ

_____፳፯..ለቋንቋ መወራረስና መዋዋስ ምክንያት ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ.ንግድ ለ.የመሬት መራድ ሐ.የተፈትሮ አደጋ መ.ሁሉም

_____፳፰.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለውይይት አቀራረብ ትክክል አይደለም።

ሀ. ሲናገሩ ድምጽን መመጠን ሐ. ተራን ጠብቆ መናገር

ለ. ርዕሱን በተመለከተ መረዳት መ. የሌሎችን ሀሳብ ማክበር

_____፳፱.በጽሑፍ ውስጥ የሰርአተ ነጥቦች ዋነኛ ተግባር _____ነው።

ሀ. የእጅ ጽሑፍ እንዲያምር ማድረግ ።

ለ. የጽሑፍ መልዕክት ሳይድበሰበስ ለአንባቢው እንደደርስ ማድረግ።

ሐ. የሚታዩ ነገሮችን መሸፈን ።

መ. ሁሉም መልስ ናቸው ።

_____፴. በጽሑፍ ውስጥ አንድን ነጠላ ሀሳብ ማስተላለፍ የሚችል የጽሑፍ ክፍል፦

ሀ. ሥርዓተ-ነጥቦች ለ. አንቀጽ ሐ. ሐረግ መ.ድርሰት

_____፴፩. አንዲትን የህይወት ዘለላ በመምረጥ ጉዳዩ የሚያደርግ የአጭር ልቦለድ መለያ ባህሪ የቱ ነው?

ሀ.ሰፊ ገለጻው ለ. ቁጥብ መቼቱ ሐ. ጥድፊያው መ. ነጠላ ውጤት

_____፴፪.ከሚከተሉት ውስጥ የአስተዋጽኦ መንደፍ ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. መልዕክትን ለማስተላለፍ ራሱን የቻለ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል።

ለ. ሐሳብን ከአላማ ጋር ለማዛመድ ያግዛል።

ሐ. ደርሰትን ከመጻፍ በፊት የሐሳብ ቅንጅትን ለማየትና ለማስተካከል ይጠቅማል።

መ. ሁሉም መልስ ነው።

_____፴፫.እንደ ፋሻ ፣ግሎብ፣ነርስ...ያሉትን ሙያዊ ቃላት በህክምና አካባቢ የምንጠቀም ከሆነ፤እንደ እንደ እሰጥ አገባ፣ ምስክር፣ አንቀጽና ቀጠሮ ያሉትን በየት አካባቢ እንገለገልባቸዋለን?

ሀ.በፍትህ ለ.በንግድ ሐ.በትምህርት መ.በግብርና

_____፴፬.አቶ በለጠ በፊው ጠፍቶበት <u>ሲዋትት</u> ዋለ።የተሰመረበት ቃል አቻ ትርጉም የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ.ሲባክን ለ.ሲያለቅስ ሐ.ሲፈራ መ.ሲርበደበድ

_____፴፭.ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ለድብልቅ ዐ.ነገር ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ.ትንቢት ከገበያ መጣች።

ለ.መማር ያስከብራል ስለዚህ ጠንክራችሁ ተማሩ።

ሐ.ፌንጣው እየዘለለ መጣ።

መ.ግቢው በአበቦች ደምቋል፤ ነፋሻማው አየር ልብን ይማርካል በአጠቃላይ ውብገጽታ አለው።

መመሪያ፭፦ከጥያቄ ቁጥር ፴፮-፴ ድረስ ለቀረቡት ቃላት ተመሣሣይ ናቸው ተብለው ከተሰጡት አማራጮች መሀከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

_____፴፮.ነሳ

ሀ ከፍ አለ ለ.ከለከለ ሐ.ቆየ መ.ነጣ

_____፴፯.አልሻም

ሀ. አልሄድም ለ.አልመጣም ሐ.አልፈራም መ.አልፈልግም

_____፴፭.ዘንግ

ሀ.ቀጭን ዱላ ለ.ወሬ ሐ.ስድብ መ.ታዋቂ

_____፴፮.የታረዘ

ሀ.የተጠማ ለ.እራቁቱን የሆነ ሐ.የተወሰነ መ.የተጨነቀ

_____፴.ወረት

ሀ.መላ ለ.ብረት ሐ.ገንዘብ መ.ጉቦ

መመሪያ ፯፦ከተራ ቁጥር ፴፩-፴፭ ድረስ የቀረቡትን ያልተማሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሊያማሉ የሚችሉትን ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ምረጡ።

_____፴፩.ጊዜ እስኪያልፍ _____

ሀ.የአባትህ ባርያ ይግዛኝ ሐ.ያንገፍግፍ

ለ.አርፈህ ተቀመጥ መ.እረፍ

_____፴፪.ረጅም ጦር _____

ሀ.ይኮሩበታል ሐ.ጠላት ያስፈራራል

ለ.ባይወጉበት ያስፈራሩበት መ.ያስከብራል

_____፴፫.ሞኝ ቢያከብሩት_____

ሀ.ያከብራል ሐ.ይኮራል

ለ.የፈሩት ይመስለዋል መ ያስፈራል

_____፴፬._____ አይገኝም ማታ

ሀ.የአፍ ወለምታ ሐ.የተመታ

ለ.የቀን ጨዋታ መ.የተረታ

_____፴፭._____ለሚመጣው አይበለጡም

ሀ.ቢከስሩም ሐ.ላይ ታች ቢሮጡም

ለ.ላለፈ አይጸጸቱም መ.ቢንከራተቱም

መመሪያ ፯፦ከተራ ቁጥር ፴፮-፴፰ድረስ ለቀረቡት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉትን ከተሰጡን አማራጮች ውስጥ ምረጡ።

_____፴፮.ልጓም በሊታ

ሀ.ቶሎ የሚቆጣ ሐ.የሰጡትን የሚበላ

ለ.በቅሎ ነጋዴ መ.ቶሎ የሚናደድ

_____፴፯.ቃሉን ሰጠ

ሀ.ተቀጣ ሐ.አስተማረ

ለ.መከረ መ.መሰከረ

_____፴፰. ሸርካታ

ሀ.ውሸታም ሐ.ስስታም

ለ.ነገረኛ መ.ፈሪ

መመሪያ ፰፦ከተራ ቁጥር ፴፱-፵፯ ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ የሚችሉትን ከተሰጡን አማራጮች ውስጥ ምረጡ።

_____፴፱. የሐሳብ ቁርኝት ያላቸውን ዐ/ነገሮች አጣጥሞ ለማቅረብ ያገለግላል።

ሀ. ነጠላ ሰረዝ ለ. ትዕምርተ ስላቅ ሐ. ትዕምርተ አንክሮ መ. ድርብ ሠረዝ

_____፱. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሥነ-ግጥምን መለያ ባህሪያትን አይወክልም።

ሀ. ምናባዊነት ለ. ምት ና ዜማው ሐ. ጥድፊያው መ. ምስል መከሰቱ

_____፲፩.ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ገፀ-ባህሪያት የሚያደርጉትን የህሳብ ልውውጥ የሚያመላክት የልቦለድ የትረካ ዘዴ

ሀ. ንግር ለ. ምልልስ ሐ. ምልሠት መ. ገፀባህሪ

_____፲፪. "--- ሁልጊዜም እንደበላህ ነው። መች ይሆን የምትጠረቃው ? የተሠመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺ

ሀ. የሚያስመስግነው ሐ. የሚወፍረው

ለ. ለሠውነት የሚያደርግለት መ. ሁሉም

_____፲፫"--- እሠን መምከር ጥቁር ዲንጋይ ላይ ውኃ እንደማፍሠስ ነው።" ይህ ህሳብ ምንን ይገልፃል?

ሀ. ደስታን ለ. ጥንካሬን ሐ. ከንቱ ልፋትን መ. ዕውቅናን

_____፲፬.ከተከታዮቹ የልቦለድ አላባውያን ውስጥ አንዱ በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ የሁነቶች ትረካ ነው።

ሀ.ግጭት ለ.ታሪክ ሐ.መቼት መ.አንጻር

_____፲፭.ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው የአንድ አካባቢን እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታን በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚቀርብ ነው።

ሀ.ተረት ለ.ሀተታ ተፈጥሮ ሐ.አፈታሪክ መ. እንቆቅልሽ

_____፲፮.ፊቷ እንደ ፀሀይ ያበራል።ይህ አ.ነገር በየትኛው የዘይቤ አይነት የተነገረ ነው?

ሀ. በአነጻጻሪ ለ.በተለዋጭ ሐ.አያዎ መ በሰዎኛ

_____፲፯.ለወትሮ ደመና ፊቱ አየጠቆረ ዓይኖቹን አሻሽቶ ያነባ ነበረ።

ይህ ግጥም የተጻፈው በየትኛው የዘይቤ አይነት ነው?

ሀ. በምጸት ለ.በሰዎኛ ሐ.በተለዋጭ መ.በግነት

መመሪያ ፲፰-ከተራ ቁጥር ፲፰-፳፫ድረስ ለቀረቡት ቅኔዎች የወርቅ ፍቺያቸውን ከተሰጡን አማራጮች ውስጥ ምረጡ።

_____፲፰.የዚህ ጠላ ነገር ጠፋ መላቅጡ፣ አሮጊቷ ናቸው የሚበጠብጡ።

ሀ.ጠላውን የሚጠምቁት አሮጊቷ ናቸው።

ለ.ሰፈሩ እርስ በእርስ እየተበጣበጠ ነው።

ሐ.የሚያጣሉት(የሚያራብሹት) አሮጊቷ ናቸው።

መ.ሰፈርተኛው ሁሉ ሰክሯል።

_____፲፱.የሰው ሁሉ አካል አድጎ ያበቃል፣ የኔማ ጣት ጉድ ነው እንደገና ያድጋል።

ሀ.የእጅ ጣቴ እያደገ ነው።

ለ.በጣም ደግ ነኝ።

ሐ.በጣም ተናድጂያለሁ።

መ.ችግሬ እየጨመረ ነው።

_____ኟ.ኧረ ለምንድን ነው ገለባ እምትገዙ፣

ያ ሳር እንደሆነ ይበቃል ለብዙ።

ሀ.መከራው ሰውን ሁሉ ያስጨንቃል።

ለ.ገለባ አትግዙ።

ሐ.ሳሩ ለከብቶች ይበቃል።

መ.ሁሉም መልስ ይሆናል።

መልካም ፈተና አዘጋጅ ማጂክ ካርፔት ት/ቤት